የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/586

ቀን ሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም.

**አማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)**

**<u>አዲስ አበባ፣</u>**

**ጉዳዩ፣ <u>የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባዔ አስመልክቶ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ስለማሳወቅ፤</u>**

መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አብን 345/02/14 በተፃፈ ደብዳቤ መጋቢት 11 ቀን 2014 ዓ.ም. በባሕር ዳር ከተማ ሙሉ አለም አዳራሽ ፓርቲው ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሁም መጋቢት 9 እና 10/2014 ዓ.ም. የተካሄደውን የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በሚመለከት ሪፖርት ማቅረባችሁ ይታወቃል።

ቦርዱ ሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች ከሕጉና ከመተዳደሪያ ደንቡ አንፃር መርምሯል።

1. የፓርቲው የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ------------- 27 ገፅ
2. የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ------------------------- 14 ገፅ
3. የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ------------- 29 ገፅ
4. 509 የጉባኤው ተሳታፊዎች የፈረሙበት ሰነድ---- 43 ገፅ

በሌላ በኩል በቦርዱ የጠቅላላ ጉባኤ ሂደት እንዲታዘቡ የተመደቡ ባለሙያዎች ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን በሪፖርታቸው ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች አረጋግጠዋል።

- በጉባኤው 581 አባላት መገኘታቸው እና ምልዐተ ጉባኤ መሟላቱ ተረጋግጦ ስብሰባው መጀመሩን፣

ለድምጽዎ የሚያምኑን



አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025
ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

- ምርጫ ቦርድ የሰጠውን መመሪያ ተከትሎ  የደንብ ማሻሻል እና የፓርቲውን የ2 ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማቅረብ የሚሉ አጀንዳዎች ከሰብሳቢዎቹ ለጉባኤው ቀርበው የጸደቁ መሆናቸውን፣

- የአመራር ለውጥ (ሪፎርም) ስለማድረግ ከጉባኤው ተሳታፊዎች በአጀንዳነት የቀረበው ሀሳብ ሰፊ ክርክር ከተደረገበት በሁዋላ በጉባኤው በአጀንዳነት መጽደቁን፣

- የመጀመሪያውን አጀንዳ በሚመለከት በአዋጅ 1162/2011 መሠረት በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ በአብላጫ ድምፅ መፅደቃቸውን፣

- ሁለተኛውን አጀንዳ በሚመለከት የፓርቲው የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርትም ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ ሪፖርቱ  በተሳታፊዎች በአብላጫ ድምፅ መፅደቁን፣

- ሦስተኛውን አጀንዳ በሚመለከት በርካታ የጉባኤ አባላት የአመራር ለውጡ በእለቱ እንዲካሄድ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን፣ ከመድረከ ጠቅላላ ጉባዔው የተዘጋጀው ምርጫ ቦርድ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት መተዳደሪያ ደንቡን አሻሽሎ በጉባኤው ለማጸደቅ እንደሆነና የአመራር ለውጥን በሚመለከት በእለቱ በአጀንዳነት ተይዞ ስላልነበረ፣ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉባኤ ተጠርቶ እንደሚከናወን ማብራሪያ መሰጠቱን፣

- ጉባኤውን ሲመሩ የነበሩት አመራሮች የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ የአመራር ለውጥ መደረግ እንዳለበት ስላመነ በጠቅላላ ጉባኤ የአመራር ለውጥ እስከሚካሄድ ድረስ በፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ላይ የአመራር ሽግሽግ ማድረጉን፣ የአመራር ምርጫ ለማካሄድ  ጊዜ ስለሚያስፈልግ ጉባኤው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ እንደሚካሄድ ቃል መግባታቸውን፣

- አስመራጭ ኮሚቴ በጉባኤው መመረጥ እንዳለበት ለአመራሩ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም መድረኩ የፓርቲው ፕሬዜዳንት በ 3 ወር ሪፎርም እንደሚደረግ ገልጠው የጉባኤውን መጠናቀቅ ተናግረው ከሌሎች የፓርቲው አመራሮች ጋር ከጉባኤው አዳራሽ ወጥተው መሄዳቸውን፣

- አብላጫ ቁጥር ያላቸው የጉባኤው አባላት የጉባኤው የአመራሮችን ከአዳራሽ መውጣት፣ የአመራር ለውጥ አለመካሄዱን እና የመድረኩን መዘጋት በመቃወም በስብሰባው አዳራሽ በመቆየት ለቦርዱ ታዛቢዎች አቤቱታቸውን እንዳሰሙ፣ "እራሳችን የአመራር ምርጫ ስለምናደርግ የምርጫ ቦርድ ታዛቢዎች ምርጫውን ታዘቡልን" የሚል ሀሳብ አቅርበው የቦርዱ ባለሙያዎች ጉባኤውን የጠራው አካል በሌለበት የሚካሄድ ምርጫ አግባብነት የሌለው መሆኑ እንደገለፁላቸው፣ ተሳታፊዎችም ይህንን ማድረግ ካልተቻለ "በድጋሚ አስቸኳይ ጉባኤ ተጠርቶ የአመራር ምርጫ እንዲካሄድ የሚያስችል የድጋፍ ፊርማ እስከምናሰባስብ ድረስ ከአዳራሽ አትውጡብን" የሚል ሌላ ጥያቄ አቅርበው ቅሬታቸውን ለቦርዱ እና ለፓርቲያቸው ማቅረብ እንደሚችሉ የገፁላቸው መሆኑን አረጋግጠው ሪፖርታቸውን አቅርበዋል።

በሌላ በኩል የጉባኤተኛ አባላት አስተባባሪ ነን የሚሉ 5 ሰዎች መጋቢት 19 ቀን 2014 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ጠቅላላ ጉባኤው ሊነጋገርባቸው ከያዛቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ አጀንዳዎች ከተጠናቀቁ በሁዋላ የአመራር ለውጥን የሚመለከተው 3ኛ አጀንዳ ሳይጠናቀቅ ሰብሳቢዎቹ ጉባኤውን ረግጠው የወጡ መሆኑን በመግለፅ ቦርዱ የነበረውን ሁኔታ በመመርመር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን በማለት ጠይቀው የ308 ሰዎች ስም እና ፊርማ የያዘ 34 ገጽ ሰነድ አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታውን አቀራረብ በተመለከተ ፊርማቸው የቀረበው ሰዎች የቀረበውን አቤቱታ ይዘት በሚያሳየው ሰነድ ላይ ያልፈረሙ በመሆኑ አስተባባሪ ነን ሲሉ የቀረቡት የጉባኤ አበላት ጥያቄ ላይ መስማማታቸውንም ሆነ ፈራሚዎቹ በእነዚህ ግለሰቦች ሊወከሉ ስለመፈለጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመኖሩ አቤቱታውን ማረጋገጥ የሚያስችል የፊርማ ማሰባሰቢያ ፎርም ቦርዱ አዘጋጅቶ ቢሰጥም አቤቱታ አቅራቢዎቹ ሳይቀበሉት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም ይህ አቤቱታ ያልተሙዋላ ይዘት ያለው ነው ሲል ቦርዱ አልፎታል።

ቦርዱ ከላይ የተብራራውን 3ኛውን በተመለከተ ጠቅላላ ጉባኤው የሄደበትን ሂደት እና ሂደቱ ከህጉ አንጻር ሊኖረው የሚገባውን ውጤት መርምሮ ተመልክቷል። ምንም እንኳን የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ያቀረበው የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔ፣ የማዕከላዊ ኮሚቴ በአጠቃላይ የአመራር ሪፎርም በተመለከተ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አመቻች ኮሚቴ ተዋቅሮ ጠቅላላ ጉባኤ ቢጠራና አጀንዳውን ቢያይ የሚለው ሀሳብ በድጋፍ ጭብጨባ /acclamation/ እንደፀደቀ ቢገልጽም የቦርዱ ታዛቢዎች አብላጫ ቁጥር ያለው የጉባኤው ተሳታፊ ይህን ድምዳሜ እንዳልተቀበለው ታዝበው በሪፖርታቸው ስላረጋገጡ ጉባኤው ያጸደቀው ይህ አጀንዳ ለጉባኤ ቀርቦ በድጋሚ ሊነጋገርበት እና ውሳኔ ሊያሳርፍበት እንደሚገባ ቦርዱ ተረድቷል።

በሌላ በኩል ተሻሽሎ የፓርቲው መተዳዳሪያ ደንብ በምርጫ አዋጁ መሰረት ከዚህ የሚከተሉትን አካቶ ሊሻሻል እና በጠቅላላ ጉባኤው ሊጸድቅ ይገባል ሲል ቦርዱ ወስኗል፡፡

ሀ/ በተሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 10 የጠቅላላ ጉባኤው ምልአተ ጉባኤ 500 እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም የፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት አጠቃላይ ብዛትን በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተገለጸ ነገር ስለሌለው አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግበት፣

ለ/ በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12.5

**"ሊቀመንበሩ የሚቀርቡለትን የስራ አስፈፃሚዎች መርምሮ በማእከላዊ ኮሚቴ ያጸድቃል"**

በሚል የተቀመጠውን በተመለከተ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከየትኛው የፓርቲው አካል እንደሚመረጡ በግልጽ ስለማያሳይ ተሻሽሎ መቅረብ ያለበት መሆኑ፤

ሐ/ በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12.11

**"ማእከላዊ ኮሚቴ ቅንጅትና ግንባርን መፍጠርን በሚመለከት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡"**

የሚለው ግንባር መፍጠርን በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀፅ 93/2/ሀ መሠረት የሚወሰነው በጠቅላላ ጉባዔ በመሆኑና የአዋጁን ድንጋጌ የሚቃረንበመሆኑ ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑ፣

መ/ በአንቀፅ 23/1/2

**"መደበኛ ጉባኤውን ለመጥራት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥም ማዕከላዊ ኮሚቴው የጉባኤውን ጊዜ እስከ 6 ወራት ሊያራዝመው ይችላል"**

የሚለው ከአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ሸ/ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ማስተካከያ በማድረግ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፣

ሠ/ በአንቀጽ 27

**"የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ አገራዊ ምርጫዎች የሚታጩበት ሥርዓት ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል"**

የተቀመጠው በአዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀፅ 74/1/ቸ መሠረት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በግልፅ በማካተት ማስተካከያ በማድረግ ማቅረብ ያለበት መሆኑ ተወስኗል፡፡

በዚሁ መሠረት፡-

1ኛ/ ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከተገለጸበት ከሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በ 2ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ሰኔ 18 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ፣

2ኛ/ ፓርቲው በደንቡ መሰረት የሚቀርጻቸውን ሌሎች አጀንዳዎችን ጨምሮ በጉባኤው የመነጋጋር መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ቀደም እልባት ያላገኘው አጀንዳ ማለትም "የአመራር ሪፎርም ወይም ለውጥ ማድረግ" የሚለው ለጉባኤው በአጀንዳነት ቀርቦ ተገቢው ውሳኔ እንዲሠጥበት እና አግባብነት ያለው ምርጫ እንዲደረግ፣

3ኛ/ ፓርቲው ከላይ ከተራ ቁጥር ሀ - ሠ የተገለፁትን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች ላይ ማሻሻያ በማድረግ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ማሻሻያ የተደረገባቸውን የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀፆች የተካተቱበት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ጉባኤው ከሚካሄድበት 5 የስራ ቀናት አስቀድሞ ለቦርዱ እንዲያቀርብ፣

4ኛ/ ከላይ የተገለፁት ማስተካከያዎች የተደረገበት እና በቦርዱ በቅድሚያ የታየ የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ በማጽደቅ እንዲያቀርብ፣

5ኛ/ ጉባኤው በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ውስጥ የጉባኤው ዝርዝር ሂደት እና ውሳኔ የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ፣ በጉባኤው የፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ እና የጠቅላላ ጉባኤውን ሪፖርት እንዲያቀርብ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን እየገለጽን ፣ቀደም ሲል በተደረገው የፓርቲው ጉባኤ ቦርዱ ሂደቱን በተሟላ ሁኔታ ለመታዘብ ይችል ዘንድ በቦርዱ የተመደቡት ባለሙያዎች ሂደቱን ለመቅረጽ ሲጀምሩ በፓርቲው አመራር የተከለከሉበት ሁኔታ ፓርቲው ሊያከብረው ከሚገባው፣ በአዋጅ 1162/11 አንቀጽ 161 መሰረት ቦርዱ አዋጁን ለማስፈጸም በሚሰራቸው ተግባራት ከቦርዱ ጋር የመተባበር ግዴታ ተጻራሪ መሆኑ ታውቆ የቦርዱ ባለሙያዎች በቀጣይ ጉባኤ የሚያደርጉትን የሙያ ትዝብት ስራ፣ አስፈላጊ በሆነ መንገድ ሁሉ (ቀረጻን ጨምሮ) ያለምንም ተጽእኖ መከወን እንዲችሉ ፓርቲው ተገቢውን እንዲፈጽም እናሳውቃለን፡፡

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ